# ኢኮኖሚያዊ ጥቃት፡አዛውንት ስደተኛ ሴቶች

ኢኮኖሚያዊ ጥቃት በማንኛውም ሁኔታ የሚከሰት የገንዘብ ቁጥጥር ፣ገንዘብ የማጥፋት፣ከገንዘብ ጉዳይ የማግለል ወይም የገንዘብ መብትን ችላ የማለት ሁኔታ ልሆን ይችላል።

ኢኮኖሚያዊ ጥቃት ማለት አንድ የሚያውቁት ሰው ፣

- ገንዘብዎን ስዎስድብዎ፣
- ገንዘብ እንድሰጡት ግፍት ስያደርግብዎ፣
- ያለርስዎ እውቅና በስምዎ የባንክ አካውንት ስከፍትብዎ፣
- እርስዎ ሳያውቁ የርስዎ የሆኑ ገንዘብ ነክ መረጃዎችን ስፈርምብዎ፣
- ፍላጎትዎን ሳይጠብቅ የቤት ውስጥ ስራ እንድሰሩ፣ልጆች እንድንከባከቡ ስያደርግዎ፣
- ገንዘቦን ተጠቅመው ምግብና ልብስ የመሳሰሉ ነገሮችን እንዳይገዙ ስከለክልዎ፣
- በገንዘብዎ የፈለጉትን ነገር እንዳያደርጉ ስከለክልዎ ነው።

ኢኮኖሚያዊ ጥቃት ማን ልያደርስብዎ ይችላል?

- ባለቤትዎ ወይም የፍቅር አጋርዎ፣
- ያደጉ ልጆችዎ፣
- የልጅ ልጆችዎ፣
- ዘመድ አዝማድዎ፣
- የምንከባከብዎት ሰዎች፣
- በአካባቢዎ ያሉ የሚያውቋዋቸው ሰዎች፣



WomanACT
WOMAN ABUSE COUNCIL OF TORONTO

ዕርዳታ ማግኘት

የኢኮኖሚ ጥቃት ስደርስብዎ በጣም የመፍራትና የተስፋቢስነት ስሜት ልሰማዎ ይችላል፡፡ነገር ግን ዕርዳታ ማግኘት ይችላሉ፡፡በራስዎ ቋንቋ ነጻና አስተማማኝ አገልግሎት ማንም ሳያውቅ የምያገኙባቸው ቦታዎች አሉ፡፡

- **211** በመደወል በአቅራቢያዎ ስላሉ አገልግሎቶች መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡
- የአዛውንቶች ደህንነት መስመር ቁጥር **(1-866-299-1011)** ደግሞ አዛውንት ሆነው መልካም ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ ካሉ ልደውሉበት ይችላሉ፡፡

1. የሚፈልጉትን ቁጥር ይደዉሉ(አገልግሎቱ በተለያዩ ቋንቋዎች በማንኛውም ቀንና ሰአት ይኖራል፡፡
2. ስልኩን ከደወሉ በኋላ የሚፈልጉትን ቋንቋ ገልጸው አስተርጓሚ ይጠብቁ፡፡
3. ስምዎትን መንገር ላይጠበቅቦት ይችላል፡፡
4. የሚፈልጉትን የዕርዳታ ዓይነት ይንገሩዋቸውና እነርሱ ምክር ይሰጡዎታል፤ወይንም ሌላ አገልግሎት ሊያገኙ የሚችሉበትን ስልክ ቁጥሮች ይሰጡዎታል፡፡

በአቅራቢያዎ ሊያገኟችው የሚችሏቸው አገልግሎቶች፤

- የገንዘብ ድጋፍ፣
- የስደተኝነት ጉዳይ፣
- የስራ ፍለጋ ጉዳይ፣
- የህግ መብት፣
- ቤት በቅናሽ የማግኘት ዕገዛ፣
- የቤት ኪራይ ድጋፍ፣
- የጤና ድጋፍ፣
- የምግብ ድጋፍ፣
- ከራስዎ አካባቢ ሰው ጋር ማገናኘት፣
- ሌሎችም.



